# መረጃዎ።

# መብቶችዎ።

# ኃላፊነቶቻችን።

የሔልዝ ፓርትነርስ አካል ለሆኑ ድርጅቶች የተዘጋጀ **የግላዊ መብት አሰራሮች ማስታወቂያ።**

ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የሚመለከት የሕክምና መረጃ እንዴት ማገልገልና ይፋ መውጣት እንዳለበትና ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ ነው።
አባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት።
**ከኖቬምበር 17 ቀን 2018 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።**

## ማጠቃለያ

ተልዕኳችን ከአባላቶቻችን፣ ታካሚዎቻችንና ከማሕበረሰቡ ጋር በመተባበር ጤናንና ደህንነትን ማሻሻል ነው። እርስዎም በሚያገኙት እንክብካቤና የጤና ሽፋን ውስጥ ድጋፍና መረጃ የማግኘት ስሜት እንዲሰማዎ እንፈልጋለን። በዚህም ውስጥ የእርስዎን መረጃ እንዴት እንደምንጠቀምና እንደምንይዝ፣ እንደዚሁም ከዚያ መረጃ ጋር የተያያዙ መብቶችዎንና ምርጫዎችዎን ማብራራትን ይጨምራል።

ግላዊ መብት ውስብስብ ርዕስ ጉዳይ ነው። በተለይም ደግሞ የተለያዩ የግዛትና የፌዴራል ሕግጋትን ማጣቀስ ስለሚያስፈልግ ጉዳዩ አደናጋሪ ሊሆን ይችላል። ለሕክምናዎ፣ ለእንክብካቤዎና ለጤና ሽፋንዎ እኛን በመምረጥ ላሳደሩብን እምነት አክብሮት አለን። መብቶችዎንና ምርጫዎችዎን እንደዚሁም የእርስዎን መረጃ እንዴት መጠቀምና ማጋራት እንዳለብን ኃላፊነታችንን ያካተተው ይህ የማጠቃለያ ክፍል ሕጉን እንዴት እንደምናከብርና የእርስዎን እምነት እንዴት እንደምናከብር እንዲገነዘቡ ያግዝዎታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

### መረጃዎ

በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ፣ "መረጃዎ" የሚለውን ቃል ስንጠቀም እርስዎን ወቅታዊ ወይም የቀድሞ የጤና እቅድ አባል አድርጎ የሚለይዎንና ከእርስዎ ጤና ወይም ሁኔታ፣ ከጤና እንክብካቤ አገልግሎትዎ፣ ከክፍያዎ ወይም ከእነዚህ አገልግሎቶች ሽፋን ጋር የተያያዘውን መረጃ መጥቀሳችን ነው። በዚህም ውስጥ የክፍያ ጥያቄና የሽፋን መረጃና የጤና መረጃ ማለትም ያገኙትን የበሽታ ምርመራና አገልግሎት የመሳሰሉ መረጃዎች ይካተታሉ። እንደ ስምዎ፣ አድራሻዎ፣ የስልክ ቁጥርዎና የትውልድ ዘመንዎ ያሉ መረጃዎችንም ያካትታል። ከእርስዎ የተገኙ መረጃዎችን ወይም እርስዎ ከእኛ፣ ከተባባሪዎቻችንና ከሌሎች ጋር በነበረዎት ግንኙነት ማለትም በምዝገባ፣ በቅድመ ፈቃድ፣ በሪፈራል፣ በሽፋን አወሳሰን፣ በክፍያ ጥያቄና በክፍያ መረጃ  ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ይጨምራል።

በአሰሪዎ በኩል የሚሰጥ ራሱን የቻለ ዋስትና ያለው እቅድ አባል ከሆኑ፣ የእርስዎን የጤና እቅድ የግላዊ መብት አሰራሮች የሚመለከቱ አብዛኞቹ መረጃዎች በአሰሪዎ በኩል የሚደርስዎ ይሆናል። እባክዎ ይህን መረጃ ለማግኘት ከአሰሪዎ ጋር ይነጋገሩ። ራሱን የቻለ ዋስትና ያለው እቅድ አባል በመሆንዎ ይህ ማስታወቂያ በሙሉ ተፈጻሚ ላይሆንብዎ ይችላል። ነገር ግን ራሱን የቻለ ዋስትና ያለው እቅድዎ የሚተዳደረው በሔልዝ ፓርትነርስ አድሚኒስትሬተርስ ኢንክ (HealthPartners Administrators, Inc.) ከሆነ፣ የዚህ ማስታወቂያ የተወሰኑ ክፍሎች እቅድዎ እንዴት በሔልዝ ፓርትነርስ (HealthPartners) እንደሚመራ ተፈጻሚ የሚሆኑብዎ ሲሆን በተለይም የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚመለከቱ መረጃዎች፡

- "መረጃዎ"
- የመረጃዎን ደህንነት የምናስጠብቅበት መንገድ ("ኃላፊነቶቻችን" በሚለው ርዕስ ስር)
- የገበያ ጥናት ("ምርጫዎችዎ" በሚለው ርዕስ ስር)
- "እቅድዎን ለመምራት" ("መረጃዎን እንዴት የምንጠቀምበትና የምናጋራበት መንገድ እንዴት ነው?" በሚለው ርዕስ ስር)

## በጤና እቅድ አባልነትዎ ያሉዎት መብቶች

**የእርስዎን መረጃና ግላዊ መብት በተመለከተ፣ በግዛትና በፌዴራል ሕጎች የተፈቀዱ ወሳኝ መብቶች አሉዎ።** ይህ ክፍልም እነዚያን መብቶች የሚያስረዳ ነው። ስለዚህ ጉዳይ መረጃ ቢጠይቁን ሂደቱን የምናስረዳዎ ሲሆን ጥያቄዎን በጽሁፍ ማቅረብ ያለብዎ ከሆነም ይህንኑ እናስረዳዎታለን።

**የሚከተለው መብት አለዎ:**

### መረጃዎን በኤሌክትሮኒክ መልክ ወይም በወረቀት ታትሞ የማግኘት

- መረጃዎ በኤሌክትሮኒክ ወይም በጽሁፍ መልክ ታትሞ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- የመረጃዎን ኮፒ ወይም ማጠቃለያ በተቻለ ፍጥነት እንዲደርስዎ እናደርጋለን።
- ልናጋራቸው  የማንችላቸው ወይም  ተደራሽነታቸውን የምንገድባቸው መረጃዎች ካሉ፣ የዚህን ምክንያት እንዲደረዱ እናግዝዎታለን።

### መረጃዎን እንድናርም መጠየቅ

- መረጃዎ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ ከሆነ ምክንያቱን ነግረውን እርማት እንድናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ።
- ለጥያቄዎ "አይሆንም" የሚል ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን፣ ነገር ግን በተቻለ ፍጥነት ምክንያታችንን እንገልጽልዎታለን። በዚህ ረገድ፣ ተቃውሞዎን (በጽሁፍ የሚያቀርቡልን መግለጫ) ከመረጃዎችዎ ጋር እንዲቀመጥልዎ ሊጠይቁን ይችላሉ።

### የምንጠቀመውን ወይም የምናጋራውን መጠን እንድንገድም መጠየቅ

- መረጃዎን እንዳንጠቀም ወይም እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ። ምንግዜም ጥያቄዎን ከግምት ውስጥ የምናስገባ ቢሆንም፣ ጥያቄዎ ለእርስዎ እንክብካቤ ወይም አገልግሎት የመስጠት ችሎታችን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ከሆነ ወይም ለውጡን በሲስተማችን ውስጥ መተግበር ካልቻልን፣ ጥያቄውን ላንቀበል እንችላለን።

### ምስጢራዊ የመልእክት ግንኙነቶችን መጠየቅ

- በተወሰነ መንገድ እንድናገኝዎ (ለምሳሌ በቤት ወይም በቢሮ ስልክ) ወይም መልእክታችንን ወደ ሌላ አድራሻ እንድንልክ ሊጠይቁን ይችላሉ።
- ፍላጎቶችዎን ለማሟላት የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። ጥያቄዎን የምንቀበለው ጥያቄውን አለመቀበላችን በእርስዎ ላይ አደጋ እንደሚያስከትል ካሳወቁን ነው።

### መረጃዎ የደረሳቸው አካላትን ዝርዝር ማግኘት

- የእርስዎን መረጃ ከሌሎች ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ለምን ያህን ጊዜ እንደተለዋወጥን፣ መረጃውን ለማን እንዳጋራንና ለምን እንዳጋራን ጭምር ዝርዝር ("አካውንቲንግ") እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- መረጃዎን ከሌላ አካል ጋር ያጋራንበትን ጊዜያት በሙሉ የምናካትት ሲሆን ይህ ግን የእርስዎን ሕክምና፣ ለሕክምናዎ ወይም ለጤና እንክብካቤ ስራዎች የከፈሉትን ክፍያ ጊዜ እና መረጃዎን ይፋ ያደረግንባቸው ሌሎች ግዜያት (ለምሳሌ መረጃውን ይፋ እንድናወጣ ጠይቀውን እኛም ስለዚሁ ጉዳይ ያሳወቅንዎ ከሆነ) አይጨምርም።

### የዚህን ማስታወቂያ ኮፒ ማግኘት

- የዚህ ማስታወቂያ የሕትመት ኮፒ እንዲሰጥዎ በማንኛውም ግዜ መጠየቅ ይችላሉ። እኛም ወዲያውኑ እንልክልዎታለን።
- ይህን ማስታወቂያ ከቀጣ ድረ ገጽ ላይም ማግኘት ይቻላል፡ healthpartners.com.

### የግላዊ መብቶችዎ ተጥሰዋል የሚል ስሜት ካደረብዎ ቅሬታ ማቅረብ

- የግላዊ መብትዎን እንደጣስንብዎ ከተሰማዎ በዚህ ማስታወቂያ የመጨረሻ ገጽ ላይ የሰፈረውን መረጃ በመጠቀም ሊያሳውቁን ይችላሉ።
- ከዚህም በተጨማሪ ቅሬታዎን ለዩኤስ የጤና ጥበቃና ሰብአዊ አገልግሎት ሚኒስቴር የሲቪል መብቶች ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ። የመ/ቤቱን አድራሻ ከዚህ ድረ ገጽ ያገኛሉ፡ **www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/complaints/**።
- ቅሬታ በማቅረብዎ በእርስዎ ላይ የሚወሰድ እርምጃ አይኖርም።

## ምርጫዎችዎ

**በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ መረጃዎን ስለምንጠቀምበትና ስለምናጋራበት መንገድ ተጨማሪ ምርጫዎች ይኖሩዎታል።** ከታች በተገለጹት ሁኔታዎች ውስጥ ምርጫ ካለዎ፣ ያሳውቁን። ምን እንድናደርግ እንደሚፈልጉ ካሳወቁን መመሪያዎን በሕጉ መሰረት እናስተናግዳለን።

**የሚከተለውን ተግባር እንዳንፈጽም ሊጠይቁን ይችላሉ፡**

- መረጃዎን ለቤተሰብዎ፣ ለቅርብ ጓደኞችዎ፣ ወይም በእርስዎ እንክብካቤ ወይም በእንክብካቤ ክፍያዎ ውስጥ ተሳትፎ ላላቸው ሌሎች አካላት እንዳናሳውቅ።
- ተልዕኳችንን ለመደገፍ የሚያስችል ገንዘብ እንዲያዋጡ እንዳንጠይቅዎ። መረጃዎን ለጤና ምርምርና ጥናት ሲባል ከሌሎች አካላት ጋር እንዳንጋራ። (ሕጉን እስካከበርን ድረስ መረጃዎን ለራሳችን ጥናትና ምርምር ተግባር ልንጠቀምበት እንችላለን።)
- ከእኛ ጋር የኮንትራት ግንኙነት ቢኖራቸውም አጋርነት ለሌላቸው የገበያ ጥናት አድራጊዎች መረጃዎን እንዳናጋራ። ከሂደቱ ለመውጣት ከፈለጉ፣ **www.healthpartners.com/optout** ድረ ገጽ ላይ ያለውን ቅጽ መሙላት ወይም ለአባላት ጉዳይ አገልግሎት በስልክ ቁጥር 952-883-5000፣ ወይም ከክፍያ ነጻ ስልክ ቁጥር 800-883-2177፣ ወይም ቲቲዋይ በስልክ ቁጥር 952-883-5127 ደውለው ማሳወቅ ይችላሉ። ለገበያ ጥናት ሲባል በቀጥታ ከሔልዝ ፓርትነርስ (HealthPartners) ወይም ከተባባሪዎቹ ወይም ከሌሎች አካላት ቀጥተኛ ጥያቄ ሊደርስዎ ይችላል፤ ይህን የምናደርገውም የአባላት እርካታ ወይም የጥራት ዳሰሳ ጥናት እንድናካሂድ በሕግ ከተጠየቅን ወይም ማረጋገጫ ለማግኘት ካስፈለገን ነው።

**የሚከተሉትን ተግባራት ከመፈጸማችን በፊት የእርስዎን ፈቃድ በጽሁፍ ማግኘት አለብን፡**

- መረጃዎን በመጠቀም ወይም በማጋራት የሌላን ድርጅት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለማሻሻጥ
- መረጃዎን በመጠቀም ወይም በማጋራት የራሳችንን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለማሻሻጥ፣ ይህም የሚሆነው ሌላ ድርጅት ይህን ተግባር እንድንፈጽም የሚከፍለን ከሆነ ወይም ምርቶቹ ወይም አገልግሎቶቹ ከጤና ጋር ግንኙነታ የሌላቸው ከሆኑ ነው።
- መረጃዎን ለሌላ ድርጅት ለመሸጥ ወይም ለማከራየት።

## ኃላፊነቶቻችን

*መረጃዎን የምንጠብቀው የእርስዎ ግላዊ መብት አስፈላጊችን በመሆኑና ሕጉም ስለሚያስገድደን ነው፡፡*

- በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ የተካተቱትን ኃላፊነቶችና የግላዊ መብት ጥበቃ አሰራሮችን መከተል አለብን፡፡
- እርስዎ አባል ሲሆኑ ይህን መረጃ የምናቀርብልዎ ሲሆን በድረ ገጽ **healthpartners.com** ላይም መለጠፍ አለብን፡፡
- ይህን ማስታወቂያ መለወጥ እንችላለን፣ ለውጦቹም እርስዎን በሚመለከት በያዝናቸው መረጃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ ጉልህ ለውጦች ካደረግን፣ አዲሱን ማስታወቂያ በድረ ገጽ ላይ የምንለጥፍ ሲሆን መረጃውንም እንልክልዎታለን፡፡
- የመረጃዎን ግላዊነት የሚጎዳ ተግባር (ያልተፈቀደ አጠቃቀም ወይም መጋራት) ሲከሰት ጉዳዩን በፍጥነት እናሳውቅዎታለን፡፡
- በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ በተገለጸው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ ወይም በጽሁፍ ፈቃድዎን ካልሰጡን በስተቀር መረጃዎን መጠቀም ወይም ማጋራት አንችልም፡፡ በማንኛውም ግዜ ሃሳብዎን መቀየር ይችላሉ፡፡ ሃሳብዎን ከቀየሩ በጽሁፍ ያሳውቁን፡፡
- መረጃዎን ከመተቀማችን ወይም ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ፈቃድ እንድናገኝ በሕግ ከተደነገገ፣ ይህንኑ ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡
- የጤና ሽፋን ልንሰጥዎ የሚገባ መሆኑን ወይም የዚህን የጤና ሽፋን ዋጋ ለመወሰን ስንል የእርስዎን ዘረ መል መረጃ አንጠቀምም፡፡
- የመረጃዎን ደህንነት እናስጠብቃለን፡፡ ወደ መረጃዎ እንዲደርሱ የምንፈቅድላቸው ሰራተኞቻችንና ሌሎች ቢሆኑም መረጃውን መጠቀም የሚችሉት ግን የእርስዎን የጤና እቅድና ጥቅማ ጥቅሞች ለማስተዳደር፣ ሕጋዊና የማረጋገጫ ግዴታዎችን ለማሟላት ወይም በሌላ መልኩ በሕግ ሲፈቀድላቸው ነው፡፡ የእርስዎን መረጃ ለመጠበቅና ያልተፈቀደ አጠቃቀምን ለመከላከል የታሰቡ አካላዊ፣ ኤሌክትሮኒክና አስተዳደራዊ ጥበቃዎችን እናደርጋለን፡፡

### ***መረጃዎን የምንጠቀምበትና የምናጋራበት መንገድ እንዴት ነው?***

*መረጃዎን የምንተቀምበትና የምናጋራባቸው መደበኛ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡*

### እርስዎን ለማከም (ሕክምና)

*መረጃዎን የምንጠቀመውና የምናጋራው ለእርስዎ ሕክምና፣ ለእርስዎ አስተማማኝና ይበልጥ የተቀናጀ የእንክብካቤ ተሞክሮ ለመፍጠር ነው፡፡*

*ምሳሌ፡ ዶክተርዎ የእርስዎን የበሽታ ዓይነትና የሕክምና እቅድ ሲልክልን ተጨማሪ አገልግሎቶችን በማመቻቸት ረገድ ድጋፍ ማድረግ እንችላለን፡፡*

እባክዎ እርስዎ በአጣዳፊ የጤና ችግር ውስጥ በመሆንዎ ምክንያት ፈቃድዎን ሊሰጡን ካልቻሉ መረጃዎን እንድናጋራ የእርስዎ ፈቃድ የማያስፈልገን መሆኑን ይገንዘቡ፡፡ በተጨማሪም፣ በዚህ ማስታወቂያ የተሸፈኑት ድርጅቶችም ለተፈቀደ አላማ እስከሆነ ድረስ መረጃዎን እርስ በርሳቸው ለመለዋወጥ የእርስዎ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም፡፡

### ለአገልግሎትዎ ለመክፈል (ክፍያ)

እርስዎ ላገኙነት የእንክብካቤ አገልግሎት ለአገልግሎት አቅራቢዎችና ለሌሎች ክፍያ ለመፈጸም መረጃዎን መጠቀምና ማጋራት እንችላለን፡፡

*ምሳሌ፡ ጥቅማ ጥቅምዎን ለማቀናጀትና ብቁነትና ሽፋንን ለማረጋገጥ ሲባል አገልግሎት አቅራቢዎችዎን ልናነጋግር እንችላለን፡፡*

### ድርጅታችንን ለመምራት (የጤና እንክብካቤ ስራዎች)

እንክብካቤዎንና ተሞክሮዎን ለማሻሻልና ስራችንን ለመምራት ስንል መረጃዎን ልንጠቀምና ልናጋራ እንችላለን፡፡

*ምሳሌ፡ ስለ እቅዱ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ስለ ሕክምና አማራጮች ወይም ስለ ጤና ነክ ምርቶችና አገልግሎቶች ልናሳውቅዎ ስንል መረጃዎን ልንጠቀምና ልናሳውቅ እንችላለን፡፡*

### እቅድዎን ለማስተዳደር

ሙሉ ዋስትና ያላቸውን ጥቅማ ጥቅሞች ለቡድን የጤና እቅድ የሚያቀርብ የጤና እቅድ፣ ወይም የራሱ ዋስትና ያለው የቡድን ጤና እቅድ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማስተዳደር ድጋፍ እንደመስጠታችን መጠን ጥያቄ ሲቀርብልን ውስን መረጃዎችን ከቡድን የጤና እቅድዎ ስፖንሰር ጋር ለእቅድ አስተዳደር አላማ ሲባል ልናጋራ የምንችል ሲሆን ለዚህም የተወሰኑ የግላዊ መብት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

*ምሳሌ፡ ሙሉ ዋስትና ላለው እቅድ፣ የተወሰኑ አኃዛዊ መረጃዎች ን ለአሰሪዎ በመግለጽ የምናስከፍለውን የአረቦን መጠን እናሳውቃለን፡፡*

የጤና እቅዳችንን በማስተዳደርና በመምራት ረገድ ድጋፍ ለሚያደርጉልን ተባባሪዎቻችን (ተዛማጅ ድርጅት ተብለውም ይጠራሉ) መረጃዎችን እናጋራለን፡፡ በተጨማሪም በእኛ ስም የተወሰኑ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከእኛ ጋር ውል ለገቡ ተባባሪ ያልሆኑ (ያልተዛመዱ) ድርጅቶች መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን፡፡ አብዛኛውን ግዜ "የንግድ ሥራ ተባባሪዎች" ብለን እንጠራቸዋለን፡፡ የንግድ ሥራ ተባባሪዎች የመረጃዎን ደህንነት ልክ እንደኛ ሆነው እንዲጠብቁ የሕግ ግዴታ አለባቸው፡፡ የንግድ ሥራ አተባባሪዎች በእኛ ስም ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል የኬዝ አመራር አገልግሎቶችና የተወሰኑ የክፍያ ተግባራት ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም ለሶስተኛ ወገኖች ማለትም ለተቆጣጣሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች፣ ለመንግስታዊ ድርጅቶች ወይም ለሕግ አስከባሪ አካላት በሕግ በሚፈቀደው ወይም በሚጠየቀው መሰረት የግል መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን፡፡

### መረጃዎን የምንጠቀምበት ወይም የምናጋራበት ሌላ መንገድ ምንድን ነው?

ከህዝብ ጤናና ከሕጋዊ ተግባራት ጋር በተያያዙ ሌሎች መንገዶች መረጃዎን እንድናጋራ ፈቃድ ወይም ግዴታ ይኖርብናል። ለእነዚህ አላማዎች መረጃዎን ከማጋራታችን በፊት በሕጉ ውስጥ የተቀመጡ በርካታ ሁኔታዎችን ማሟላት አለብን።

## ሕጉን መከተል

- በግዛት ወይም በፌዴራል ሕግ ከተገደድን መረጃዎን መጠቀም ወይም ማጋራት እንችላለን።

## ከሕዝብ ጤና አጠባበቅና ከደህንነት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ድጋፍ መስጠት

መረጃዎን ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ባለስልጣናት ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድርጅቶች የምናጋራባቸው የተወሰኑ ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ሁኔታዎች መካልም:

- በሽታ ለመከላከል
- ምርቶች ወደአምራቹ ተመልሰው እንዲሰበሰቡ ለማገዝ
- በሕክምና ላይ የሚኖሩ አሉታዊ ውጤቶችን ሪፖርት ለማድረግ
- በእንክብቤ መስጫ ቦታዎቻችን ውስጥ የሚታይ ጥቃት፣ ቸልተኝነት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ወይም ወንጀሎችን ሪፖርት ለማድረግ
- በማንኛውም ሰው ጤና ወይም ደህንነት ላይ የተጋረጡ ከባድ ስጋቶችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ
- እንደ ኦዲት ወይም ምርመራዎች ባሉ የጤና ስርዓት ቁጥጥሮች ላይ ድጋፍ ለመስጠት
- እንደ ውትድርና፣ ብሄራዊ ደህንነት፣ ፕሬዝዳንታዊ የጥበቃ አገልግሎቶችና ለማረሚያ ተቋማት የሚደረጉ የመረጃ አሰጣጥን የመሳሰሉ ልዩ መንግስታዊ ተግባራትን ለመፈጸም

## ለሰውነት አካል ወይም ለሕብረ ሕዋስ ልገሳ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት

- ከሰውነት አካል ወይም ከሕብረ ሕዋስ ልገሳ ጋር በተያያዘ መረጃዎን ልንጠቀምና ልናጋራ እንችላለን።

## ከሕክምና መርማሪ ወይም ከቀብር ዳይሬክተር ጋር ተባብሮ መስራት

- መረጃዎን የአሟሟት ሁኔታ ለሚያጠና አካል፣ ለሕክምና መርማሪ፣ ወይም ለቀብር ዳይሬክተር እናጋራለን።

## የሠራተኞችን የካሳ ጉዳይ ማስተናገድ

- የሠራተኞችዎን የካሳ ጥያቄ ለማስተናገድ መረጃዎን እንጠቀማለን፣ እንዲሁም እናጋራለን

## ለክስና ሕጋዊ እርምጃዎች ምላሽ መስጠት

- ለሕጋዊ እርምጃዎች ወይም ፍ/ቤት ወይም አስተዳደራዊ ትዕዛዝን ለመፈጸም ወይም ሌሎች ሕጋዊ ሂደቶችን ለመፈጸም ሲባል መረጃዎን እንጠቀማለን፣ እንዲሁም እናጋራለን።
- አግባብነት ላላቸው የሕግ አስከባሪ ኃላፊዎች መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን።

## የእርስዎን የጽሁፍ ፈቃድ በማግኘት

- መረጃዎን በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ባልተሸፈነ መንገድ ለመጠቀም ወይም ለማጋራት ከፈለግን፣ በቅድሚያ የእርስዎን የጽሁፍ ፈቃድ ማግኘት ይኖርብናል።

## መረጃ ለመጠየቅ፣ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ

ስለ ጤና እቅድ አሰራሮቻችንና ስለ ግላዊ መብቶችዎ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወደ ሔልዝ ፓርትነርስ (HealthPartners) የአባላት አገልግሎት ክፍል በስልክ ቁጥር **952-967-5000**፣ ከክፍያ ነጻ ስልክ ቁጥር **800-883-2177** ወይም በስልክ ቁጥር **952-883-5127** (ቲቲዋይ) መደወል ይችላሉ። ይህን መረጃ በድረ ገጽ **healthpartners.com** ማግኘትም ይችላሉ። በተጨማሪም ለሔልዝ ፓርትነርስ (HealthPartners) የሐቀኝነትና ደንብ አከባበር ክፍል በስልክ ቁጥር **1-866-444-3493** መደወል ይችላሉ።

**የሔልዝ ፓርትነርስም (HealthPartners) ታካሚ ነዎት?**

ስለ እንክብካቤ አሰጣጥ የግል መብት አሰራሮቻችን ማንኛውም ጥያቄ ቢኖርዎ እባክዎ እንክብካቤ በሚያገኙበት ቦታ ያነጋግሩን። በተጨማሪም በቀጣዩ አድራሻን በስልክ ሊያነጋግሩን ይችላሉ፡

ሔልዝ ፓርትነርስ (HealthPartners) የሐቀኝነትና ደንብ አከባበር ክፍል በስልክ ቁጥር 1-866-444-3493 ወይም ፓርክ ኒኮሌት ስልክ ቁጥር 1-855-246-PNHS (7647)

## አደረጃጀታችን

ይህ ማስታወቂያ በሁሉም ድርጅቶቻችንና አቅራቢዎቻችን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል*:

- Amery Hospital & Clinics
- Capitol View Transitional Care Center
- Group Health Plan
- HealthPartners Administrators (as the administrator of self-insured health plans)
- HealthPartners Dental Group and Clinics (including Three Rivers Dental Care and Three Rivers Orthodontics)
- HealthPartners Hospice and Palliative Care
- HealthPartners Insurance Company
- HealthPartners Medical Group and Clinics
- Hudson Hospital & Clinic
- Hutchinson Health
- Lakeview Hospital
- North Suburban Family Physicians
- Olivia Hospital & Clinics
- Park Nicollet Clinic
- Park Nicollet Health Care Products
- Park Nicollet Melrose Center
- Park Nicollet Methodist Hospital
- Regions Hospital
- RHSC
- Riverway Clinics
- TRIA Orthopaedic Centers and Clinics
- virtuwell®
- Westfields Hospital & Clinic
- በዚህ ዝርዝር ውስጥ ከተካተቱት ድርጅቶች መካከል በየትኛውም ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ የሕክምና ሰራተኞች
- በዚህ ዝርዝር ውስጥ ከተካተቱት ድርጅቶች መካከል በየትኛውም የሚሰጡ የስፔሻሊቲ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች
- በሆስፒታሎቻችን የተደራጁ የጤና እንክብካቤ ዝግጅቶች ውስጥ የሚሳተፉ የግል አገልግሎት አቅራቢዎች ወይም ኮንትራክተሮች፡፡

ከጁን 1 ቀን 2022 ጀምሮ

* ድርጅታችን በተለወጠና ባደገ ቁጥር ይህ ዝርዝር ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለወጥ ይችላል፡፡ በ **healthpartners.com** ድረ ገጽ ላይ በተለጠፈው ማስታወቂያ ውስጥ ያለውን ዝርዝር እናሻሽላለን፡፡

# ለጤና እቅድ አባላት ፀረ መድልኦን የሚመለከት መግለጫ

**የእኛ ሃላፊነቶች፡**

የፌዴራል ህዝባዊ መብት ህጎችን እንከተላለን በዘር፡በቀለም፡በትውልድ ሀገር፡ በእድሜ፡ በአካል መጉደል ወይም በጾታ ላይ ተመርኩዞን መድልኦ አንፈጽምም:: በዘር፡በቀለም፡በትውልድ ሀገር፡ በእድሜ፡ በአካል መጉደል ወይም በጾታ (በፈለጉት ጾታ መታወቅን አጠቃሎ) ላይ ተመርኩዞን ሰዎችን አናገልም ወይም በተለየ መልኩ አናስተናግድም::

**አካለስንኩልነት ያለባቸው ሰዎች ከኛ ጋር እንዲግባቡ እንረዳቸዋለን:: ይህ እርዳታ ነጻ ነው:: የሚያጠቃልለው፡**

- ብቃት ያላቸው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን
- በሌሎች ቅርፀቶች የተዘጋጁ የጽሁፍ መረጃዎች፣ለምሳሌ ትልልቅ ህትመቶች፡ በድምጽ እና ኮምፒዉተር ላይ የሚገኙ ቅርፀቶች ናቸው

**እንግሊዝኛ ለማይናገሩ ወይም እንግሊዝኛ መናገር ለሚከብዳቸዉ ሰዎች አገልግሎቶች እንሰጣለን:: እነኚህ አገልግሎቶች ነጻ ናቸው:: እነሱ የሚያጠቃልሉት፡**

- ብቃት ያላቸው አስተርጓሚዎችን
- በሌሎች ቋንቋዎች የተፃፉ መረጃዎችን በተመለከተ

**ለቋንቋ ወይም የመገናኛ እርዳታ፡**

የቋንቋ ወይም ሌላ የመገናኛ እርዳታ ካስፈለግዎት 1-800-883-2177 ይደውሉ:: (TTY: 711)

**መድልኦን የሚከለክል መርሃችንን አስመልክቶ ጥያቄ ካለዎት፡**

1-844-363-8732 ወይም
integrityandcompliance@healthpartners.com
ከህዝባዊ መብቶች ሰብሳቢ ጋር መገናኘት ይችላሉ::

**አቤቱታ ለማቅረብ፡**

በእርስዎ ዘር፡ቀለም፡ የትውልድ ሀገር፡ እድሜ፡ አካለስንኩልነት ወይም ጾታ ምክንያት እነዚህ አገልግሎቶች አልተሰጡኝም ወይም መድልአ አድርጋችሁብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ በ 1-844-363-8732, integrityandcompliance@healthpartners.com ወይም ለCivil Rights Coordinator, Office of Integrity and Compliance, MS 21103K, 8170 33rd Ave S., Bloomington, MN 55425 በመጻፍ ከህዝባዊ መብቶች አቀናባሪ ጋር ተገናኝተው  አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ::

በተጨማሪ በህዝባዊ መብቶች አቤቱታ ማቅረቢያ ቢሮ (Office for Civil Rights Complaint Portal) ድረ ገጽ  https://ocrportal.hhs.gov/ocr/portal/lobby.jsf jsf  አማካይነት፣ ወይም ከዚህ ተከትሎ ባለው የፖስታ አድራሻ ወይም በስልክ ለአሜሪካ የጤና እና ማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ (U.S. Department of Health and Human Services)፣ የህዝባዊ መብቶች ቢሮ (Office for Civil Rights) ህዝባዊ የመብቶች አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፣

U.S. Department of Health and Human Services
Room 509F, HHH Building
200 Independence Avenue SW, Washington, DC 20201
1-800-368-1019, 800-537-7697 (መስማት ለተሳናቸው)(TDD)

| | |
|---|---|
| Español *(Spanish)*<br>ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-800-883-2177. (TTY: 711) | ພາສາລາວ *(Laotian)*<br>ໂປດຊາບ: ຖ້າວ່າ ທ່ານເວົ້າພາສາ ລາວ, ການບໍລິການຊ່ວຍເຫຼືອດ້ານພາສາ, ໂດຍບໍ່ເສັຽຄ່າ, ແມ່ນມີພ້ອມໃຫ້ທ່ານ. ໂທຣ 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| Hmoob *(Hmong)*<br>LUS CEEV: Yog tias koj hais lus Hmoob, cov kev pab txog lus, muaj kev pab dawb rau koj. Hu rau 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Deutsch *(German)*<br>ACHTUNG: Wenn Sie Deutsch sprechen, stehen Ihnen kostenlos sprachliche Hilfsdienstleistungen zur Verfügung. Rufnummer: 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| Tiếng Việt *(Vietnamese)*<br>CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-800-883-2177. (TTY: 711) | العربية *(Arabic)*<br>ملحوظة: إذا كنت تتحدث اذكر اللغة، فإن خدمات المساعدة اللغوية تتوافر لك بالمجان. اتصل برقم 1-800-883-2177 (رقم هاتف الصم والبكم: 711) |
| 繁體中文 *(Chinese)*<br>注意：如果您使用繁體中文，您可以免費獲得語言援助服務。請致電 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Français *(French)*<br>ATTENTION: Si vous parlez français, des services d'aide linguistique vous sont proposés gratuitement. Appelez le 1-800-883-2177. (ATS: 711) |
| Русский *(Russian)*<br>ВНИМАНИЕ: Если вы говорите на русском языке, то вам доступны бесплатные услуги перевода. Звоните 1-800-883-2177. (телетайп: 711) | 한국어 *(Korean)*<br>주의: 한국어를 사용하시는 경우, 언어 지원 서비스를 무료로 이용하실 수 있습니다. 1-800-883-2177. (TTY: 711) |

| | |
|---|---|
| Af Soomaali *(Somali)*<br>OGAYSIIS: Haddii aad ku hadasho afka soomaaliga, Waxaa kuu diyaar ah caawimaad xagga luqadda ah oo bilaash ah. Fadlan soo wac 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Tagalog *(Tagalog)*<br>PAUNAWA: Kung nagsasalita ka ng Tagalog, maaari kang gumamit ng mga serbisyo ng tulong sa wika nang walang bayad. Tumawag sa 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| Oromiffa *(Cushite [Oromo])*<br>XIYYEEFFANNAA: Afaan dubbattu Oromiffa, tajaajila gargaarsa afaanii, kanfaltiidhaan ala, ni argama. Bilbilaa 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Italiano *(Italian)*<br>ATTENZIONE: In caso la lingua parlata sia l'italiano, sono disponibili servizi di assistenza linguistica gratuiti. Chiamare il numero 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| አማርኛ *(Amharic)*<br>ማስታወሻ: የሚናገሩት ቋንቋ ኣማርኛ ከሆነ የትርጉም እርዳታ ድርጅቶች፣ በነጻ ሊያግዝዎት ተዘጋጀተዋል፡ ወደ ሚከተለው ቁጥር ይደውሉ 1-800-883-2177. (መስማት ለተሳናቸው: 711) | ภาษาไทย *(Thai)*<br>เรียน: ถ้าคุณพูดภาษาไทยคุณสามารถใช้บริการช่วยเหลือทางภาษาได้ฟรี โทร 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| unD *(Karen)*<br>ဟ်သူဉ်ဟ်သး– နမ့ၢ်ကတိၤ ကညီ ကျိာ်အဃိ, နမၤန့ၢ် ကျိာ်အတၢ်မၤစၢၤလၢ တလၢာ်ဘူဉ်လၢာ်စ့ၤ နီတမံၤဘဉ်သ့န့ဉ်လီၤ. ကိး 1-800-883-2177. (TTY: 711) | ελληνικά *(Greek)*<br>ΠΡΟΣΟΧΗ: Αν μιλάτε ελληνικά, στη διάθεσή σας βρίσκονται υπηρεσίες γλωσσικής υποστήριξης, οι οποίες παρέχονται δωρεάν. Καλέστε 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| ខ្មែរ *(Mon-Khmer, Cambodian)*<br>ប្រយ័ត្ន៖ បើសិនជាអ្នកនិយាយ ភាសាខ្មែរ, សេវាជំនួយផ្នែកភាសា ដោយមិនគិតឈ្នួល គឺអាចមានសំរាប់បំរើអ្នក។ ចូរ ទូរស័ព្ទ 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Diné Bizaad *(Navajo)*<br>Díí baa akó nínízin: Díí saad bee yáníłti'go **Diné Bizaad**, saad bee áká'ánída'áwo'dę́ę́', t'áá jiik'eh, éí ná hólǫ́, kojį' hódíílnih 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| Deitsch *(Pennsylvanian Dutch)*<br>Wann du Deitsch schwetzscht, kannscht du mitaus Koschte ebber gricke, ass dihr helft mit die englisch Schprooch. Ruf selli Nummer uff: Call 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Ikirundi *(Bantu – Kirundi)*<br>ICITONDERWA: Nimba uvuga Ikirundi, uzohabwa serivisi zo gufasha mu ndimi, ku buntu. Woterefona 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| Polski *(Polish)*<br>UWAGA: Jeżeli mówisz po polsku, możesz skorzystać z bezpłatnej pomocy językowej. Zadzwoń pod numer 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Kiswahili *(Swahili)*<br>KUMBUKA: Ikiwa unazungumza Kiswahili, unaweza kupata, huduma za lugha, bila malipo. Piga simu 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| हिंदी *(Hindi)*<br>ध्यान दें: यदि आप हिंदी बोलते हैं तो आपके लिए मुफ्त में भाषा सहायता सेवाएं उपलब्ध हैं। 1-800-883-2177. (TTY: 711) | 日本語 *(Japanese)*<br>注意事項：日本語を話される場合、無料の言語支援をご利用いただけます。1-800-883-2177 (TTY: 711) まで、お電話にてご連絡ください。 |
| Shqip *(Albanian)*<br>KUJDES: Nëse flitni shqip, për ju ka në dispozicion shërbime të asistencës gjuhësore, pa pagesë. Telefononi në 1-800-883-2177. (TTY: 711) | नेपाली *(Nepali)*<br>ध्यान दिनुहोस्: तपाईंले नेपाली बोल्नुहुन्छ भने तपाईंको निम्ति भाषा सहायता सेवाहरू निःशुल्क रूपमा उपलब्ध छ । फोन गर्नुहोस् 1-800-883-2177 (टिटिवाइ: 711) |
| Srpsko-hrvatski *(Serbo-Croatian)*<br>OBAVJEŠTENJE: Ako govorite srpsko-hrvatski, usluge jezičke pomoći dostupne su vam besplatno. Nazovite 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Norsk *(Norwegian)*<br>MERK: Hvis du snakker norsk, er gratis språkassistansetjenester tilgjengelige for deg. Ring 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| ગુજરાતી *(Gujarati)*<br>સુચના: જો તમે ગુજરાતી બોલતા હો, તો નિ:શુલ્ક ભાષા સહાય સેવાઓ તમારા માટે ઉપલબ્ધ છે. ફોન કરો 1-800-883-2177. (TTY: 711) | Adamawa *(Fulfulde, Sudanic)*<br>MAANDO: To a waawi Adamawa, e woodi ballooji-ma to ekkitaaki wolde caahu. Noddu 1-800-883-2177. (TTY: 711) |
| اُردُو *(Urdu)*<br>خبردار: اگر آپ اردو بولتے ہیں، تو آپ کو زبان کی مدد کی خدمات مفت میں دستیاب ہیں ۔ کال کریں 1-800-883-2177 (TTY: 711). | Українська *(Ukranian)*<br>УВАГА! Якщо ви розмовляєте українською мовою, ви можете звернутися до безкоштовної служби мовної підтримки. Телефонуйте за номером 1-800-883-2177. (телетайп: 711) |



23676 (6/2022) Amharic